# FY26 የካፒታል በጀት እና 2025-30 የካፒታል ማሻሻያ ፕሮግራም የቀረቡ ማሻሻያዎችን በተመለከተ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ መግለጫ

**ኦክቶበር 23, 2024**

በዚህ ሳምንት መጀመሪያ ላይ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ (ቦርድ) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስን (MCPS) ሱፐርኢንተንደንት ተቀብሎ አነጋግሯል። [recommendations for the Fiscal Year (FY) 2026 Capital Budget and amendments to the FY 2025-2030 Capital Improvement Program (CIP)]

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስን (MCPS) ሱፐርኢንተንደንት ዶ/ር ቶማስ ቴለር ለቦርዱ ባቀረቡት ሀሳብ፣ ቀደም ሲል በዲስትሪክቱ የተፈፀመው ስህተት አሁን ለ 2026 በጀት ዓመት የካፒታል በጀት ላይ እጥረት እንዲፈጠር አስተዋፅዖ ማድረጉን አስረድተዋል።

የ 2026 የካፒታል በጀት በ $1.853 ቢሊዮን ዶላር ተወስኖ ይቀራል፣ነገር ግን ዲስትሪክቱ ለሥራ የሚያስፈልገውን $39.3 ሚሊዮን የባጀት እጥረት በከፊል ለመሸፈን $21.6 ሚሊዮን ዶላር በካውንቲው እንዲሸፈን ይፈልጋል። እጥረቱ የተከሰተው ለቻርለስ W. ውድዋርድ "Charles W. Woodward project" ፕሮጀክት የስቴት ዕርዳታ ስሌት ላይ በተፈጠረ ስህተት ነው። አንዳንዶቹ እጥረቶች CIP የገንዘብ ድጋፎችን በማቀናነስ ሊቀረፉ ይችላሉ፣ነገር ግን የቻርለስ W. ውድዋርድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ኖርዝዉዉድ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት፣ ክራውን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እና ወሳኝ የሆኑ HVAC መሠረተ ልማትን ሥራ ለማጠናቀቅ የገንዘብ ድጋፍ ማግኘት ያስፈልጋል።

የትምህርት ቦርድ በሱፐርኢንተንደንቱ ቡድን ስህተቱን ማግኘታቸውን እና ጉዳዩን በግልፅ ማቅረባቸውን ያደንቃል። እንደነዚህ ያሉት ስህተቶች ህዝቡ በዲስትሪክቱ ላይ ያለውን እምነት ያዳክማሉ። እነዚህን ጉዳዮች ወደ ብርሃን ማምጣት፣ የማስተካከያ እርምጃ እንድንወስድ እና ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ያለንን ራዕይ የሚደግፍ መወሰድ ያለበትን ቀጣይ እርምጃ ለመወሰን በጣም አስፈላጊ ነው።

ቦርዱ ከ MCPS አዲስ አመራር ጋር በቅርበት በመስራት በዲስትሪክቱ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚፈጥሩ ጉዳዮችን ለመከላከል እና የውስጥ ቁጥጥርን ለማጠናከር ቁርጠኛ ነው። ዶ/ር ቴለር እና ቡድናቸው ለጋራ ግቦቻችን ቀጣይነት ያለው ማሻሻል ለማድረግ፣ ለግልጽነት፣ እና ለተጠያቂነት ቁርጠኛ ናቸው።

የእኛ ትልቁ ሀላፊነት አሁን ያሉት የትምህርት ቤቶች ፕሮጀክቶች በሰዓቱ እንዲጠናቀቁ እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ተማሪዎችን ፍላጎት እንዲያሟሉ ማድረግ ነው። ይህንን መሰናክል ለመጋፈጥ እና ለተማሪዎች ስኬት የሚደግፍ የትምህርት መሠረተ ልማት ለመዘርጋት ቦርዱ የካውንቲውን ድጋፍ ይጠይቃል።

በዚህ ጉዳይ ቦርዱ ከማህበረሰቡ ጋር ለመሥራት የተያዘው ጊዜ ኦክቶበር 24 ነው። ኖቬምበር 4 እና 6 ሁለት ህዝባዊ መድረኮች ይካሄዳሉ። በማህበራዊ መድረኮች ላይ ለመናገር/ሃሳብ፣ አስተያየት ለመስጠት ኦክቶበር 24 እኩለ ቀን ላይ ምዝገባ ክፍት ይሆናል። የበለጠ ለማወቅ፣ አስተያየት ለመስጠት፣ ለመናገር፣ ለመመዝገብ የትምህርት ቦርድን [ድረ ገጽ] ይጎብኙ።

የትምህርት ቦርድ ስለ በጀት ዓመት FY 26 የካፒታል በጀት እና CIP ማሻሻያ ላይ ኖቬምበር 21 እርምጃ ይወስዳል።